# <u>መቅድም</u>

እኛ በሎስ እንጀለስና አካባቢው የምንኖር ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮ እሜሪካውያን በራሳችን ፈቃድ በአዲስ መልክ በመደራጀት የማህበረሰባችንን ችግሮች በጋራ ለመቋቋም ድንቅ የሆኑ የጋራ ባህላዊ ዕሴቶቻችንን ለመጠበቅ ከምንኖርበት አገር ባህል ህግና የኑሮ ዘይቤ በማጣጣም ውጤታማ እንድንሆን በሁለንተናዊ መልኩ የሚያግዝ ከማንኛውም የዘር የፖለቲካና የሐይማኖት አመለካከት ልዩነቶች ነፃ የሆነ ጠንካራ ማህበር እንዲኖረን በመፈለግና እንዲሁም የእርስ በእርስ የመቀራረብ፣ የመግባባት፣ የመረዳዳትና የመተጋገዝ ባህላችንን በማዳበርና በአሁኑ ጊዜም ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው በግልም ሆነ በድርጅት መልክ የተለያዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ያሉትን በአንድ ላይ አስተባብሮና አዋህዶ በመያዝ ሰፋ ያለ የተሻለ ውጤታማ የሆነ አገልግሎቶችን ለመስጠት እንድንችል በማሰብ ሁሉን አቀፍ የሆነ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስን ለማቋቋም ይህን የመተዳደሪያ ደንብ (Bylaw) በዛሬው ቀን --------አፅድቀናል

## <u>ምዕራፍ አንድ፡- ምሥረታ (ESTABLISHMENT)</u>

**<u>አንቀጽ 1፡- ስያሜ</u>** የማህበሩ መጠሪያ ስም "የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎሰንጀለስ" (ETHIOPIAN COMMUNITY LOS ANGELES.( E . C. L. A) ተብሎ ይጠራል

**<u>አንቀጽ 2፡- የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን</u>** ይህ ደንብ በሎስ አንጀለስ ከተማ እና በሌሎች በአካባቢው በሚገኙ ከተሞች ውስጥ በሚኖሩ የማህበሩ አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል

**<u>እንቀጽ 3፡- የማህበሩ የሥራ ቋንቋ አማርኛና እንግሊዘኛ ይሆናል</u>**

**<u>አንቀጽ 4፡- አድራሻ</u>** የማህበሩ ዋና ጽሕፈት ቤት በሎስ አንጀለስ ከተማ ይሆናል

**<u>አንቀጽ 5፡- ትርጓሜ</u>** በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ

**<u>5.1 ኢትዮ አሜሪካዊ ፡-</u>** ማለት በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆኖ በዜግነት አሜሪካዊ የሆነ ወይም የሆነች የማህበሩ አባል ነው።

**<u>5.2 ሎስ አንጀለስ እና አካባቢው፡-</u>** ማለት በሎስ አንጀለስና አካባቢው በሎሰንጀለስ ፣ኦሬንጅ ሳንበርናንዲኖ፣ ሪቨርሳይድና ቬንቹራ ካውንቲ ውስጥ በሚገኙ ከተሞች የሚኖሩ የማህበሩ አባላት ነው

**<u>5. 3 አባል፡-</u>** ማለት የአባልነት መመዘኛውን በማሟላት ግዴታውንም በአግባቡ የሚወጣ ሰው ሲሆን ይህም በሁሉም የማህበሩ የሥራ ሀላፊነት ተመርጦ የሚያገለግሉትንም ያጠቃልላል።

**<u>5.4 ቤተሰብ</u>** ፡- ማለት የአባሉ ወይም የአባሏ የትዳር ጓደኛ ልጆች

አብርዋቸው የሚኖሩ አባት ወይም እናት ናቸው



**<u>5.5</u> <u>ማህበር</u>**፡- ማለት የኢትዮጵያ ማህበረ ሰብ ማህበር በሎስ አንጀለስ ማለት ነው

**5.6 ኢ . ማ . ሎ አ፦** የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ ማለት ነው

**5.7 ጠቅላላ ጉባኤ** ፦ ማለት የአባልነት መመዘኛውንና ግዴታውን የተወጣ መላውን አባላት የሚያካትት፡ ሲሆን የማህበሩ ወሳኝ የበላይ አካል ነው

**5.8 ቦርድ፦** ማለት በጠቅላላው ጉባኤው አጠቃላይ ስብሰባ የሚመረጥ 11 አባላትን ያካተተ አካል ነው

**5.9 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፦** ማለት በቦርዱ የሚመረጡ ወይም የሚመድቡ የማህበሩን የዕለት ከዕለት የሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውኑ ናቸው

**5.10 ዳይሬክተር፦** ማለት በቦርድ የሚመርጥ ወይም የሚቀጠር የሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ በሀላፊነት የሚመራና ማህበሩን የሚወክል ነው

## ምዕራፍ ሁለት፦ዓላማ (OBJECTIVES)

**አንቀጽ 6፦የማህበሩ ዓላማዎች** የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ (E. C. L A) የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. በሎስ አንጀለስና አካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮ-አሜሪካውያን በመቀራረብ የጋራ ባህሎቻቸውንና ታሪካቸውን እንዲያዳብሩ ምቹ የጋራ መድረኮችን ለመፍጠር
2. የሐይማኖት የፆታ የፖለቲካ የብሔርና የዕድሜ ወዘተ ልዩነት ሳይኖር ማንኛውም የማህበሩን ደንብ የተቀበለ/ች ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮ-አሜሪካዊ የሆነን ሁሉ አንድ ጠንካራ የሆነ ማህበረሰብ (Community) በማቋቋም የጋራ መብትን ለማስከበር ይቻል ዘንድ ድርጅታዊ ሃይል ለመፍጠር፣ በሞት በሕመም ፣በአደጋ በሥራ እጦትና በአካል መጓደል ችግር ለሚገጥማቸው እና እንዲሁም አዲስ ለሚመጡ ኢትዮጵያውያን ያለ ብዙ ችግር በቀላሉ ወደ አሜሪካን የአኗኗር ዘይቤ እንዲሸጋገሩ የሚያስችለውን ዘዴ ለማመቻቸት
3. የማህብረሰቡ አባላትና ቤተሰብ ለጤናማ አኗኗር የጋራ አገልግሎት መጠቀሚያ የሚሆን የትምህርት ስልጠና፣ የአካል ማደበሪያና የመዝናኛ ወዘተ በአጠቃላይ ሁሉን አቀፍ የሆነ የማህበረ ሰብ (COMMUNITY) ማዕከል መፍጠር
4. የማህበረሰባችን ወጣቶች ከአጉል ባህል ከወንጀል ከአልባሌ ሱስ ነፃ እንዲሆኑ የምክር የስልጠናና መልሶ የማቋቋሚያ ድጋፍና ዕርዳታ ለመስጠት
5. በህብረሰባችን ውስጥ ለሚገኙ አዛውንት ( እናትና አባት ) የሚውሉበት የሚዝናኑበት አገልግሎት ማመቻቸት
6. በሎስአንጀለስና አካባቢው የሚኖሩ በማህበረሰባችን አባሎች ላይ የሰብአዊ መብት የፍትህ መጓደል ቢከሰት በጋራ ችግሩን ለመቋቋምና ለመከላከል ወጣቶች የነፃ ትምህርት ዕድልና ማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እገዛና ድጋፍ ለመስጠት

በማህበረሰብቻን ውስጥ የሚገኙትን የህክምና ፕሮፌሽናልና እንዲሁም የማህበራችን ወዳጆች የሆኑትን ሐኪሞች ጭምር ዕውቀታቸውን የሚጠይቅ ቅድመ ዝግጅት አዘል የሆነ ትምህርትና ዕርድታ ማዘጋጀት

7. የማህበረሰባችንን ወጣት ልጆች በአዕምሮ መታወክ በኦቲዝም፣ በካንሰር እንዲሁም በመሳሰሉት ህመሞች እንዴት መከላከልና ማዳንም ጭምር የያዘ ትምህርት ማዘጋጀት

## <u>ምዕራፍ ሶስት፡- የማህበሩ የገቢ ምንጭ</u>

<u>አንቀጽ7፡-የገቢ ምንጭ</u> ማህበሩ አላማውን ለማሳካት የሚጠቀምባቸው የገቢ ምንጭ፣

1. ከመህበሩ አባላት የሚሰበሰብ የመመዝገቢያና አመታዊ የአባልነት ክፍያ

2. የተለያዩ ዝግጅቶችን ተግባራዊ በማድረግ ከሚገኝ ገቢ

3. የፕሮጀክት ሀሳቦችን በማመንጨት መንግስታዊና ለጋሽ ለሆኑ ድርጅቶች

በማቅረብ ከሚገኝ የገንዘብ ድጎማ

4. ከበጎ አድራጊ ግለሰቦችና ከማህበሩ አባላት የሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡

<u>**አንቀጽ 8፡- የአባላት የገንዘብ አስተዋጽዖ መጠን**</u> የማህበሩን ደንብ ተቀብሎ የኢትዮጵያ ማህበረ ሰብ በሎስ አንጀለስ አባል ለመሆን ፈቃደኛ የሆነ ሰው፡ የአባልነት መመዝገቢያ ክፍያ በግለሰብ $10.00 በቤተሰብ $15.00 ይከፍላል።

1. አያንዳንዱ የተመዘገበ የማህበሩ አባል ዓመታዊ ክፍያ በግለሰብ $40.00 በቤተሰብ $60.00 ሲሆን፡ ክፍያው አቅምና ፍላጎት ያለው በአንድ ጊዜ መክፈል ይችላል
2. ባንድ ጊዜ መክፈል ካልተቻለ በሩብ ዓመት (በ የ4 ወሩ) በግለሰብ $10.00 በቤተሰብ $15.00 በመክፈል የአመቱን ክፍያውን ያጠናቅቃል፡ የክፍያ፡ ወራቶች
   የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ክፍያ **January (1-10)**
   የሁለተኛው ሩብ ዓመት ክፍያ **April (1-10)**
   የሶስተኛው ሩብ ዓመት ክፍያ **July (1-10**
   የአራተኛው ሩብ ዓመት ክፍያ **Oct (1-10)** ድረስ ይሆናል

3. የአሜሪካ ህግ በሚደነግገው መሰረት በጡረታ የተገለሉ የማህበሩ አባላት የመመዝገቢያና ዓመታዊ ክፍ አምሳ በመቶ ቅናሽ (50% discount) አላቸው

## <u>ምዕራፍ አራት ፡- አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር (Organizational Structure, Powers and Duties</u>

<u>**አንቀጽ 9፡- ጠቅላላ ጉባኤ**</u> ጠቅላላ ጉባኤ የኢትዮጵያ ማህበረ ሰብ በሎስ አንጀለስ ዓላማ ለማራመድ የአባልነት ግዴታቸውን የሚወጡ አባላትን በሙሉ ያካተተ ስብስብ ሲሆን የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት

ይኖሩታል።

1. ወሳኝ የሆኑና በደንቡ ላይ የተመለከቱትን የማህበሩ ጉዳዮች የመጨረሻው ወሳኝ አካል ነው
2. የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላትና አስራ አንድ የቦርድ አባላትን ይመርጣል
3. በዓመት አንድ ጊዜ በመሰብሰብ ከሥራ አሰፈጻሚ ኮሚቴው ከቦርዱ ከኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ የሚቀርብለትን የሥራ አፈጻጸምና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዳምጦ ውሳኔና መመሪያ ይሰጣል፤
4. የቦርዱ ሊቀ መንበር አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ከጠራ ይሰበሰባል፤
5. የተጓደሉ የሥራ መስኮች ካሉ በቦታው በምርጫ ይተካል
6. ዓመታዊ ባጀት ያፀድቃል አፈጻጸሙም ሕግና ደንብ የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል መተዳደሪያ ደንቡን ያጸድቃል አስፈላጊ ሲሆን ያሻሽላል
7. ከማሕበሩ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ (50%) በስብሰባ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡ምልአተ ጉባኤ ካልተሟላ ግን በእለቱ ከተገኙት ውስጥ ¾ ( 75%) የእለቱ አጀንዳ እንዲቀጥል ከወሰኑ ስብሰባው ይካሄዳል ይሁን እንጂ በዕለቱ በስበሰባው ላይ የተገኙት አባላት ከጠቅላላ አባላት ቁጥር ቢያንስ ከ10% (ከአስር ከመቶ) በላይ መሆን ይኖርበታል።

**<u>እንቀጽ 10፡- ቦርድ</u>** የኢትዮጵያን ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ ቦርድ በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ አስራ አንድ (11) አባላት ይኖሩታል የማህበሩ ጠቅላላ የሥራ ክንውን የመተዳደሪያ ደንቡን ተከትሎ መከናወኑን የሚያረጋግጥ የበላይ አካል ሲሆን ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆና ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም፣

1. ቦርዱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚያደርገው የሥራ እንቅስቃሴ የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፡
2. የማህበሩ ንብረቶችና ገንዘብ በአግባቡ መያዙንና በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡
3. የሥራ አስፈጻሚ አባላትን ይመርጣል፡
4. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚያደርጋቸው የውጭ ግንኙነቶች ከማህበሩ ዓላማ ጋር የማይፃረሩ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፡
5. በሥራ እስፈጻሚ ኮሚቴው የሚቀርብለትን የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ፣ ባጀት ፣ የፕሮጀክት ሃሳቦችን ( Project proposals) መርምሮ ያጸድቃል፡
6. በየሶስት ወሩ በመስብሰብ፡ የማህበሩን የሥራ አንቅስቃሴ ሪፖርት ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያዳምጣል እርማትና የማስተካከያ መመሪያ ይሰጣ የቦርዱ አባላት ማህበሩ የሚጠናከርበትን አባላት ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ዘዴ በማጥናትና በመከታተል ማሻሻያ ያደርጋል፡
7. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የቋሚና የጊዜያዊ ሠራተኞች ቅጥርና የክፍያ መጠን ሲያቀርብ ያፀድቃል፡ ይህ ተግባራዊ የሚሆነው ማህበሩ በቂ የገንዘብ አቅም ሲኖረው ነው ፡
8. ከኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ መተዳደሪያ ደንብ በማይፃረር መንገድ ቦርዱ የራሱን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፡
9. ከ $3000.00 ( ከሶስት ሺ) በላይ የሚጠይቁ ወጭዎችን ያጸድቃል፡
10. እንደ አስፈላጊነቱ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው እንዲፈርሱ ያደርጋል፡
11. የሥራ ዘመኑ ሲያልቅ ወጭ ቦርድ ከአዲሱ ከገቢው ቦርድ ጋር ለመጀመሪያው ስድስት ወራት አብሮ በመሳተፍ የሽግግር ወቅቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ትብብር ያደርጋል።

**አንቀጽ 11፡- የቦርድ ሊቀመንበር** የቦርድ ሊቀ መንበር በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለቦርዱና ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል፣ ዝርዝር ተግባሩና ህላፊነቱም፣

1. የቦርዱን ስብሰባ በሊቀ መንበርነት ይመራል
2. የጠቅላላ ጉባኤን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል ስብሰባውን በሊቀ መንበርነት ይመራል
3. የቦርዱ አባላትና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባለት በህገ ደንቡ መሰረት ተግባራቸውን ማከናውናቸውን ያረጋግጥል
4. የቦርድ አባላትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንዲሁም ዳይሬክተሩ ሃላፊነታቸውን በብቃትና በትጋት እንዲወጡ ያበረታታል
5. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ዳይሬክተሩ የመተዳደሪያ ደንቡን በመከተሉ በተለያዩ ኮሚቴዎች ምደባ ያዘጋጃል፡ በቦረዱ አባላት ሲፀድቅ በተግባር ያውላል፣

**አንቀጽ 12፡- የቦርድ ምክትል ሊቀ መንበር** ምክትል ሊቀመንበሩ በተቅላላ ጉባኤው ይመረጣል ተጠሪነቱ ለቦርዱና ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል ተግባርና ሃላፊነቱም፡

1. የምክትል ሊቀ መንበሩ የሥራ ድርሻ ከሊቀ መንበሩ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ ሊቀ መንበሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሊቀመንበሩ በምትኩ ሥራውን ያከናውናል
2. በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን የማስተባብርና የመቆጣጠር ተግባራት ያከናውናል

**አንቀጽ 13 ፡- የቦርድ ፀሐፊ** በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን፣ተጠሪነቱም ለቦርዱና ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል፣ የሚከተሉት ተግባርና ህላፊነት ይኖሩታል።

1. ከሊቀመንበሩ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የቦርድ ስብሰባና አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል
2. የቦርዱንና የጠቅላላ ጉባዔውን የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል
3. በማንኛውም የቦርድ ስብሰባ ወቅት ያለፈውን ቃለ ጉባኤ በማንበብ እንዲፀድቅ የደርጋል
4. የቦርዱን የጽ/ ቤት ተግባራት ያከናውናል መዛግብትና መረጃዎችን ይይዛል
5. የማሕበሩን አባላት ዝርዝር መዛግብት ይይዛል
6. ወጭና ገቢ ደብዳቤዎችን ያዘጋጃል በሊቀ መንበሩ ሲፈረም ወደሚመለከተው ይስተላልፋል
7. በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ማንኛውንም ተጨማሪተግባራት ያከናውናል፣

**አንቀጽ 14፡- የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ** የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለተቅላላ ጉባኤውና ለቦርዱ ነው የሚከተሉት የሚከተሉት ሃላፊነትና የሥራ ድርሻ ይኖሩታል።

የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በህዝብ፣ መገናኛ ብዙሃን ፣ በበራሪ ወረቀቶች ፣በሬዲዮንና በኢንተርኔት ሚዲያዎች የሚሰራጩ መረጃዎችን የሚያቀናብርና ለሕዝብ የሚያስተላልፍ ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባኤውና ለቦርዱ ይሆናል።

1. የማህበሩ አላማና የሥራ እንቅስቃሴ ለህዝብ መገናኛ ብዙሃን ያሰራጫ የማህበሩን ድረገጽ (Web-Site) ያስተዳድራል ወቅታዊ መረጃዎችን ያስቀምጣል፡
2. የጠቅላላ ጉባኤውን የቦርዱንና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ስብሰባ በቭዲዮ በመቅረጽ ፋይል ያደርጋል፡
3. የኮሚቴዎችን አቢይ የሥራ እንቅስቃሴ በቭዲዮ በመቅረጽ ለህዝብ የሚተላለፍበትን መንገድ ያዘጋጃል፡
4. የማህበሩን እንቅስቃሴ ለአባላት ለማሰራጨት በየ 6 ወሩ መጽሄት ያዘጋጃል ያሰራጫል፡
5. ለሥራው እንቅስቃሴ የሚያስፈለጉትን ቁሳቁሶች ዝርዝርና ባጀት ያቀርባል ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያውላል፡፡
6. በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚመለከታቸውን ሃላፊዎች ቃለ መጠየቅ በማድረግ ለአባላት የሚሰራጭ፡ መረጃዎችን አቀነባብሮ ያዘጋጃል፡
7. በኮሚቴው ውስጥ በፈቃደኝነት አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉትን በመመልመል በኮሚቴው ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያውላል፡
8. ማንኛውም የጽሁፍ የኤሌክትሮሪኒክስ፡ የቃለ መጠይቅ፡ መግለጫዎች፡ ሁሉ ከመተላለፋቸው በፊት በዳይሬክተሩ መፈቀዱንና የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፡

   አባላትን በማስተባበር ረገድ አስፈላጊ የሆኑትን ተግባራት በተገቢ መልኩ ይከታተላል ያስፈጽማል

**አንቀጽ 15 ፡-ገንዘብ ያዥ** የማህበሩ ገንዘብ ያዥ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤውና ለቦርዱ ይሆናል ዝርዝር ተግባርና ሀላፊነቱም የሚከተሉት ናቸው።

1. የማሕበሩን ገንዘብ ገቢና ወጭ በሚዛናዊ የገንዘብ አያያዝ ዘዴ በመጠቀም ይቆጣጠራል
2. የማሕበሩ አባላት የመመዝገቢያና አመታዊ ክፍያ እንዲፈጽሙ ክትትል ያደርጋል
3. ማንኛውንም የገንዘብ ወጭ ከመፈረሙ በፊት የወጭ ማዘዣ ሰነድ በዳይሬክተሩ ወይም በቦርድ የተፈቀደና የተፈረመ መሆኑን ያረጋግጣል
4. ማንኛውም ወደ ማህበሩ የሚላክ ወይም የሚገባ ገንዘብ በማሕበሩ ትክክለኛ ደረሰኝ ተመዝግቦ ለላኪው ወይም ለከፋዩ እንዲደርስ ያደርጋል ደረሰኙም የማሕበሩ አርማ ያለበትና የቁጥር ቅደም ተከተል የያዘ መሆኑን ያረጋግጣል
5. ከማንኛውም የገቢ ምንጭ የተሰበሰበ ገንዘብ በ24 ሰአት ውስጥ ወደ ማሕበሩ ባንክ ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል

**<u>አንቀጽ 16፡- የኦዲት ቁጥጥር ኮሚቴ</u>** የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጡ 3 የሂሳብ የንብረትና አስተዳደር ሙያተኞችን ያቀፈ ሲሆን ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም፣

1. የማሕበሩን የገንዘብ የሂሳብና የንብረት አያያዝ ደንብ በማዘጋጀት በቦርዱ ሲፀድቅ ለሚመለከታችው የሥራ ክፍሎች ያስተላልፋል
2. የሥራ አስፈፃሚው የገንዘብና የሂሳብ ኮሚቴ ገንዘብና ሂሳብ በደንቡ መሠረት መከናውናቸውን በየ 6 ወሩና በማንኛውም ጊዜ እንዳስፈላጊነቱ የቁጥጥር ሪፖርት ያቀርባል፣
3. በአመት አንድ ጊዜ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርት ለቦርዱ፣ ለሥራ አስፈፃሚና ለጠቅላላ ጉባኤያው ይቀርባል፣
4. እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ የገንዘብም ሆነ የሥራ አፈፃፀም ምርመራና ኦዲት በማድረግ ለቦርዱ ወይንም ለጠቅላላ ጉባኤው ያሳውቃል፣
5. የቦርዱና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሥራ ዘመኑ ከመጠናቀቁ ከ 2 ወር በፊት የኦዲት ሪፖርት ያዘጋጃል የርክክብ ሰነድ በማዘጋጀት አዲስ ገቢዎችና ነባሮች እንዲፈራረሙ ያደርጋል፣
6. የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሁሉም የስራ ክፍሎች በተግባር ላይ መዋሉን፣ ዕቅዶችና ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ባጀትና የጊዜ ገደብ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣

**<u>አንቀጽ 17፡- የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ</u>** የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በቦርዱ የሚመረጥና የማህበሩን የዕለት ከዕለት ሥራ የሚያከናውን ሲሆን ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል

1 አባላትን ይመዘግባል የአባላትን ዝርዝር መረጃ ይይዛል።
2 የማህበሩን የአለት ከለት የሥራ አንቅስቃሴ ያከናውናል፡
3 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ ሕጋዊ ወኪል ሲሆን፡ ማህበሩን በመወከል የውጭ ግንኙነት ተግባራትን ያከናውናል ይደራደራል
4 ማህበሩን የሚያጠናክሩ ዕቅዶችን በመንደፍ በቦርዱ ሲፀድቅ በተግባር ያውላል፡
5 በየሶስት ወሩ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት በጽሁፍ ያዘጋጃል ለቦርዱ ያቀርባል፡.
6 የማህበሩ አባላት በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ተገቢውን አገልግሎት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል ግዴታቸውንም እንዲወጡ ክትትል ያደርጋል
7 የማህበሩን ዓመታዊ ባጀትና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፡ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፡
8 በቦርዱ የፀደቁትን የቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች ቅጥር ያስፈጽማል ያስተዳድራል፡
9 የማህበሩን ዓላማ ለመተግበር የገንዘብና የቁሳቁስ ፍላጎት ለማሟላት የተለያዩ የገንዘብና ማቴሪያል ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን በመንደፍ በቦርዱ ሲፀድቅ በተግባር ያውላል፡

10 እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ የገንዘብም ሆነ የሥራ አፈፃፀም ምርመራና ኦዲት በማድረግ ለቦርዱ ወይንም ለጠቅላላ ጉባኤው ያሳውቃል፣

11 የቦርዱና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሥራ ዘመኑ ከመጠናቀቁ ከ 2 ወር በፊት የኦዲት ሪፖርት ያዘጋጃል የርክክብ ሰነድ በማዘጋጀት አዲስ ገቢዎችና ነባሮች እንዲፈራረሙ ያደርጋል፣

12 የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሁሉም የሥራ ክፍሎች በተግባር ላይ መዋሉን፣ ዕቅዶችና ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ባጀትና የጊዜ ገደብ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣

13 የማህበሩ አባላት በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ተገቢውን አገልግሎት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል ግዴታቸውንም እንዲወጡ ክትትል ያደርጋል

14 የማህበሩን ዓመታዊ ባጀትና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፡ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፡

15 በቦርዱ የፀደቁትን የቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች ቅጥር ያስፈጽማል ያስተዳድራል፡

16 የማህበሩን ዓላማ ለመተግበር የገንዘብና የቁሳቁስ ፍላጎት ለማሟላት የተለያዩ የገንዘብና ማቴሪያል ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን በመንደፍ በቦርዱ ሲፀድቅ በተግባር ያውላል፡

17 እንዳስፈላጊነቱ ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን በማቋቋም አጣዳፊ ሥራዎች እንዲከናወኑ ለቦርዱ በማቅረብ ሲጸድቅ ተግባር ላይ ያውላል፡

18 የማህበሩ ገንዘብ ንብረትና መረጃዎች በጥንቃቄ መያዛቸውን ያረጋግጣል፡

19 ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ በማድረግ የየኮሚቴዎችን የሥራ እንቅስቃሴ ይገመግማል መመሪያ ይሰጣል፡

20 በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ የሚገኙት የኮሚቴ አስተባባሪዎች፣ ዋና ጸሐፊውና ዳይሬክተሩ ሲሆኑ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሌሎች የኮሚቴው አባላት ሊጋበዙ ይችላሉ፡

21 ከ $3000.00 በላይ ወጭ የሚጠይቁ ክፍያወችን በቦርዱ እንዲፀድቅ ለቦርዱ ያቀርባል ሲጽድቅ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡

22 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ የሚጠራውና የሚመራው በዳይሬክተሩ ሲሆን ከኮሚቴ አባላት መካከል 1/2 ኛ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡

**<u>አንቀጽ 18፡- ዳይሬክተር</u>** የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ በምርጫ ወይም በቅጥር በቦርድ ይመደባል ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሲሆን ዝርዝር ሀላፊነቱም፣

1. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል ያስተዳድራል፡
2 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን በሊቀ መንበርነት ይመራል፡
3. በቦርድ አባላት ስብሰባ ላይ ይሳተፋል ድምፅ ግን መስጠት አይችልም፡
4. ማህበሩን በመወከል የውጭ ግንኙነት ያደርጋል ይደራደራል፡

5. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ይተሰጣቸውን የሥራ ሀላፊነት በብቃት መወጣታቸውን ያረጋግጣል ይከታተላል፡

6.የሥራ እቅዶችና ፕሮጀክቶች በጊዜው መፈጸማችውን ይቆጣጠራል፡

7. በኮሚቴ አባላት መካከል መልካም የሥራ ምክክርና መግባባት እንዲፈጠር ያበረታታል፡

8. የመሕበሩ ገንዘብና ንብረት በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፡ የተዝረከረከ አሰራርና ብክነት ሲታይ አስቸኳይ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡

9. የሥራ ማስኪያጃና ለማህበሩ ተግባር በወጭ ማዘዣ ደብዳቤ ለሂሳብና ፋይናንስ ኮሚቴ አስተባባሪ ይልካል በባንክ ቼክ ላይም ይፈርማል

10. የኮሚቴውን አባላት የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ በሚመለከት የውስጥ መመሪያ ያዘጋጃል፡

11. በኮሚቴ አባላት አብዛኞቹ (50%) ሲስማሙበትና በቦርዱ ሲጸድ በተገባር ላይ ያውላል፡

12. ሌሎች በቦርዱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡

**<u>አንቀጽ 19፡- ዋና ፀሐፊ</u>** ዋና ፀሐፊው በምርጫ ወይም በቅጥር በቦርድ ይመደባል ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ይሆናል ዝርዝር ተግባሩና ሀላፊነቱም፡የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ጽ/ቤት ያስተዳድራል፡

1. የወጭና ገቢ ደብዳቤዎችን ይቀበላል ለሚመለከታቸውም የሥራ ክፍሎች ያሰራጫል በቅደም ተከተል ፋይል ያደርጋል፡
2. የማህበር አባላትን ዝርዝር መረጃ በሚገባ ይይዛል ይጠብቃል
3. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ስብሰባ እንዲጠራ ዳይሬክተሩ ሲፈቅድ ይጠራል፡ የስብሰባውን ቃለ ጉባኤ ይይዛል በቅደም ተከተል መረጃውን ፋይል ያደርጋል፡

የማህበሩ ጽ/ቤት ለአባላት ክፍት እንዲሆን ዕቅድ በማውጣት በኮሚቴው ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡

4. የጽ/ቤት ቁሳቁሶችን ፍላጎት ዝርዝር በመስራት በጀት ይጠይቃል፡

7. የየኮሚቴዎችን የሥራ ፕሮጀችት ዕቅዶች በተወሰነላቸው የጊዜ ገደብና በጀት መከናወናቸውን በመከታተል ለዳይሬክተሩ ሪፖርት ያቀርባል፡

8. ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፡

9. ዳይሬክተሩ በማይኖር ጊዜ ዳይሬክተሩን ተክቶ ይሠራል

**<u>አንቀጽ 20፦ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም</u>**

የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ በሎስ ኝጀለስ ቦርድ ወይም የሰራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማንኛውንም ሥራ በጊዛዊነት ወይም በቋሚነት ለማሠራት ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ ኮሚቴ ወይም ንኡስ ኮሜቴ ማቋቋም ይችላሉ የኮሚቴው ተጠሪነትና ተግባር ፡

1. ለማንኛውም ተግባር የሚቋቋም ኮሚቴ ግብረ ፣ሀይል ወይም ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ላቋቋመው አካል ይሆናል
2. የህግና የማህበራዊ ጉዳይ የጤናና የስፖርት የትማህርትና የስልጠና፣ የሴቶችና የህጻናት፣ የወጣቶችና የአዛውንት ጉዳይ ኮሚቴ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ችሎታና ፍላጎት ያላቸው ሰዎችን በመጋበዝ እንዲያቋቁሙ፡ይደረጋል፡፡
3. ቦርድ ማንኛውንም ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ወይም ግብረሀይል አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው ማፍረስ ይችላል።
4. **<u>አንቀጽ 21፦ የእቅድና ፕሮጀክት ጥናት ኮሚቴ</u>** የዕቅድና ፕርጀክት ጥናት ኮሚቴ በቦርድ የሚቋቋም ሲሆን በስሩ የእቅድና የባጀት የፕሮጀክት ሀሳብ ጥናት ሙያተኞችን በመመልመል የማህበሩን ያጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድና ባጀት ያዘጋጃል የፕሮጀከት ሃሳቦችን ያዘጋጃል ተጠሪነቱም ለዳይሬክተሩ ሲሆን ዝርዝር ተግባረና ሀላፊነቱም

1. ከሁሉም ኮሚቴዎች የሚቀርቡ ፍላጎቶችን በማቀናጀት የማሕበሩን ዓመታዊ በጀትና ዓቅድ ያዘጋጃል
2. የማሕበሩን ዕድገትና ፍላጎት ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የረጅም ጊዜ የሥራ እቅድ ያዘጋጃል
3. የፕሮጀክት ሃሳቦችን ያመነጫል በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና በቦርዱ ሲፈቀድ ዝርዝር ጥናት በማዘጋጀት ለለጋሽ ድርጅቶች ( Donors ) መላኩን ይከታተላል
4. የተፈቀዱ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ይከታተላል ለለጋሽ ድርጅቶች የአፈፃፀም ሪፖርት በሰምምነቱ መሰረት በጊዜው መላኩን የከታተላል።
5. ማህበሩን ሊደግፉ የሚችሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ዝርዝር በማጥናት ሲፈቀድ ፕሮጀክቶች ተዘጋጅተው እንዲላኩ ያድርጋል
6. 6ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ስራዎች ያከናውናል

**<u>አንቀጽ 22፦ የሕግና ማሕበረዊ ጉዳይ ኮሚቴ</u>** የሕግና ማሕበራዊ ጉዳይ ኮሚቴ በቦርድ የሚቋቋም ሲሆን በሥሩ የቤተሰብ ችግር ጉዳይ -የኢሚግሬሽን ሕግ ጉዳይ ሙያተኞችን በፈቃደኝነት በመመልመል ለማህበሩ አባላት ሰፊ አገልገሎት የሚሰጥ ክፍል ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው ዝርዝር ተግባሩና ሀላፊንቱም፡

በስራ እጦት በጤና ምክንያት በዕድሜ በጾታና በመሳሰሉት ችግሮች ሰለባ የሆኑ የማሃበሩ አባላት ተገቢውን ድጋፍና ምክር እንዲያገኙ የድርጋል፡

1. ችግር ቢያጋጥማቸው አባላት ተገቢውን እርዳታና ድጋፍ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግኑኝነት ያደርጋል

2. አዲስ ለሚመጡ ኢትዮጵያውያን ከአካባቢው ጋር እንዲተዋወቁ የምክር የሞራል የስራ ማፈላለግ ምክርና ጥቆማ ካስፈልገም ችግር ላለባቸው የገንዘብና የማቴርያል ድጋፍ እንዲያገኙ በማጥናትና ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያውላል፡
3. ለራሳቸውም ሆነ ለቤተሰቦቻቸው የኢሚግሬሽን ችግር ለሚኖርባቸው ምክርና አገልግሎት ይሰጣል፡
4. እንደ አስፈላጊነቱ በአካባቢው የሚደረጉ ኢትዮጵያን የሚመለከቱ በአላትን ያዘጋጃል ዝግጅቱንም በሃላፊነት ይመራል፡
5. ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፡

<u>**አንቀጽ 23፡- የጤናና የስፖርት ኮሚቴ**</u> የጤናና ስፖርት ኮሚቴ በቦርድ የሚመረጥ ሲሆን በስሩ ፈቃደኛ የሆኑ ሐኪሞች ነርሶችና የስፖርት ባለሙያዎችን በማሰባሰብ ለማህበሩ አባላት አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ የሚያመቻች ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም

1 የማህበሩ አባላት የጤና ችግሮች ትምህርትና መግለጫ በማዘጋጀት በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ያሰራጫል ያስተምራል
2 በአካባቢያችን የሚታዩ የጤና ችግሮችን በማጥናት ተገቢውን የመከላከያ የመቆጣጠሪያ መረጃ ለአባላት ይሰጣል
3 በተለያዩ ምክንያቶች ህክምና ለማግኘት ችግር ያለባቸው አባላት በነጻ እርዳታ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል አቅም ላላቸው ግሩፕ ኢንሹራንስ በቅናሽ፡ የሚያገኙበትን ሁኔታ በማጥናት መረጃ ይሰጣል
4 <u>**አንቀጽ 24፡- የትምህርትና ሥልጠና ኮሚቴ**</u> የትምህርትና ስልጠና ኮሚቴ በቦርድ የሚመረጥ ሲሆን ለሥራው ፈቃደኛ የሆኑ የኮምፒተር ስልጠና የቋንቋ ማሻሻያ (እንግሊዘኛና አማርኛ) ለወጣቶች የሚሰጥ ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም፣
    1. አዲስ ለሚመጡ አባላት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ማሻሻያ ስልጠና ይሰጣል፣
    2. የኮምፒተር ስልጠና ለሚሹ አባሎች ስልጠና ይሰጣል፣
    3. ለወጣቶችና ሕፃናት የአማርኛ ማንበብና መጻፍ ስልጠና ይሰጣል፡
    4. የኢትዮጵያን ልዩ ባሕልና ታሪክ ለወጣቶች ትምህርት ይሰጣል፣
    5. ለሥራው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ዝርዝርና በጀት ያዘጋጃል

<u>**አንቀጽ 25፡- የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ኮሚቴ**</u> የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ኮሚቴ አስተባባሪ በቦርድ የሚመረጥ ሲሆን በስሩ ሁለት ፈቃደኛ ረዳቶችን በመመልመል በሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ላይ ያተኮሩ ሥራወችን ያከናዉናል ተጠሪነቱም ለዳይሬክተሩ ነው ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም ፣

1. የማህበሩ አባል የሆኑ ሴቶች በፆታቸው ምክንያት የሚደርስባችው ችግሮች ካሉ ጥቆማ በመቀበልና በማጥናት ድጋፍና እርዳታ እንዲያገኙ ማድረግ፣
2. ሴቶች እንዲደራጁ ማበረታታት፣
3. ሴቶች በሚሠሩበት ቦታና በሚኖሩበት አካባቢ የሚደርስባቸውን በደል የምክር ካስፈለገም የህግ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፣

4. ሴቶች የሃገራቸውን ባህልና ሙያ የሚያንፀባርቁ ተግባራትን በጋራ እያዘጋጁ ለአካባቢው ህዝብ እንዲያሳውቁ ያደርጋል፣
5. አቅም  የሌላቸውና በሥራ ላይ የተሰማሩ ወላጆች የሕፃናት መዋያ፣ ከትምህርት ቤት መልስ ማቆያ አገልግሎት መስጫ እንዲኖር ዕቅድ ያወጣል ሲፈቀድና በባጀት ሲደገፍ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡
6. ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሥራወች ያከናውናል

<u>**አንቀጽ 26 ፡- የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ**</u> የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ በቦርድ  የሚቋቋም ሲሆን፣ በሥሩ ሁለት ወጣቶችን በመመልመል በወጣቶች ጉዳይ ላይ ያተኮሩ ሥራወችን ያከናውናል ተጠሪነቱም ለዳይሬክተሩ ነው ዝርዝር ተግባሩና ሃላፊነተም፣

1. ወጣቶች የማህበሩ አባል እንዲሆኑ ይቀሰቅሳል ያበረታታል፣
2. ወጣቶች ከኢትዮጵያ ባህል ጋር እንዲተዋወቁና ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋል፣
3. ወጣቶች ከጎጂ ባህልና ልምድ እንዲርቁ ቅስቀሳና መረጃ ይሰጣል ለወጣቶች መልካም አርአያ
4. የሚሆኑ ጎበዝ ተማሪ ዎችን ፣ስፖርተኞችን ወዘተ በመጋበዝ ጥሩ ሞዴል እንዲሆኑ የወጣቶችን ስብሰባ በማዘጋጀት በመገናኛ ብዙሃን ያስተዋውቃል፣
   ወጣቶች ባህላቸውን አክባሪ ቤተሰባቸውንና ወገናቸውን አፍቃሪ እንዲሆኑ የማበረታቻና የኪነጥበብ ዝግጅቶችን ያቀነባብራል፣
5. ፈቃደኛ የሆኑ ወጣቶች ለህፃናትና በትምህርት ሂደት ችግር ላለባቸው በትርፍ ጊዜአቸው ትምህርት እንዲሰጡ ያደርጋል ያስተባብራል፤

<u>**አንቀጽ 27፡- የአዛውንት ጉዳይ አስተባባሪ ኮሚቴ**</u> የአዛውንቶች ጉዳይ አስተባባሪ ኮሚቴ በቦርድ የሚቋቋም ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነት የኖሩታል

1. የአዛውንት እንክብካቤ ማዕከል እንዲኖር ያደርጋል ለማዕከሉ የሚያስፈልጉትን ቅድመ ዝግጅት ያመቻቻል
2. ለአዛውንቶች አስፈላጊውን  የአካል ጥንካሬና  የሞራል ማበረታቻ  ትምሕርታዊ  ምክር ይሰጣል
3. በሕመም ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ችግር ሲያጋጥማቸው ተከታትሎ በመጠየቅ የሞራል ብርታት እንድያገኙ ጥረት ያደርጋል  ያበረታታል

## <u>ምዕራፍ አምስት፡- አባልነት (MEMBERSHIP)</u>

<u>**አንቀጽ 28፡- የአባልነት መመዘኛ**</u> የማህበሩ አባል ለመሆን የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት ይኖርበታል፡

1. ኢትዮጵያዊ ወይንም ኢትዮ-አሜሪካዊ የሆነ/ች ወይንም በጋብቻ የተሳሰሩ
2. የማህበሩን  መተዳደሪያ ደንብ ተረድቶ የተቀበለና የአባልነት ማመልከቻ የሞላ/ች
3. የመመዝገቢያና ዓመታዊ ክፍያ ያጣጠናቀቀ/ች
4. በዕድሜ ከ18 ዓመት በላይ የሆነ/ች

**አንቅጽ 29፡- የአባላት መብት** በመተዳደሪያ ደንብ መሠረት በእኩል የማህበሩ አገልግሎቶች ተጠቃሚ የመሆን፣ በስብሰባ ላይ ያለምንም ገደብ ሃሳቡን የመግለጽ

1. አመራሮቹን በደንቡ መሠረት ለመምረጥና ለመመረጥ
2. በህመም በአደጋ በሥራ ማጣት ወዘተ ችግር ምክንያት የመመዝገቢያና ዓመታዊ ክፍያ ለመክፈል አቅም ያለመኖር ሲገጥም በነጻ የማህበሩ አባል የመሆን

**አንቀጽ 30፡- የአባላት ግደታዎች** በስብሰባ ላይ የመገኘት

1. የመተዳደሪያ ደንብን የማክበር
2. ዓመታዊ መዋጮውን በደንቡ መሠረት የመፈጽም
3. የማህበሩን ንብረቶችና መገልገያዎች በአግባቡ የመጠቀም
4. ያለክፍያ የማህበሩ አባል የሆነ/ች ነፃ የኮሚኒቲ አገልግሎት የመስጠት
5. **አንቀጽ 31፡- ከአባልነት የሚያሰግዱ ድርጊቶች** አንድ አባል በአንቀጽ 28 ላይ የተዘረዘሩትን የአባልነት ግዴታዎች ያለበቂ ምክንያት ለሶስት ተከታታይ ጊዜያቶች ማከናወን ከተሳነው፡ ከአባልነት ይወገዳል

1. አንድ አባል ከአባልነት ከመወገዱ በፊት በቅድሚያ የጎደለውን እንዲያሟላ ሁለት ጊዜ ከሥራ አስፈጽሚ ኮሚቴው የጽሁፍ ማሳሰቢያ ከጊዜ ገደብ ጋር ይላክለታል በተሰጠው የጊዜ ገደብ ካላሟላ ከአባልነት መሰርዙን የሚገልጽ ደብዳቤ ይላክለታል፡
2. አንድ አባል ከአባልነት ሲሰናበት የከፈለው ክፍያ አይመለስለትም
3. ከአባልነት ከተሰረዘ በኋላ እንደገና ለመመዝገብ የሚያመለክት አባል $30.00 መቀጫ በመክፈል ለሁለተኛ ጊዜ እንዲመዘገብ የመጨረሻ እድል ይሰጠዋል፡
4. አንድ አባል የግሉን የፖለቲካ የሐይማኖት የብሔር ወዘተ አመለካከት በሌሎች አባሎች ላይ ተጽእኖ ካደረገና በማስረጃ ከተረጋገጠ ከአባልነት ይወገዳል፡
5. ማሕበሩ ላልተመዘገበና ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት በአባልነት ግዴታውን ለማይወጣ አባል አገልግሎት ለመስጠት ግዴታ አይኖርበትም፡

## ምዕራፍ ስድስት ፡-ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች (MISCELENOUS PRROVISIONS)

**አንቀጽ 32፡- የምርጫና የድምጽ አሰጣጥ ሥነ ስረዓት** ከማንኛውም ምርጫ በፊት ተገቢውን የአባልነት መስፈርት መሟላታቸውንና በማህበሩ እንቅስቃሴ የሚሳተፉ አባላት ለመምረጥም ሆነ ለመመረጥ ብቃት ያላቸው ምሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡

1. አባላት የምርጫ ድምጽ የሚሰጡት በጽሁፍ ለምርጫው በተዘጋጀ ካርድ በሚስጢር ይሆናል
2. ቦርዱ ምርጫው በትክክል እንዲካሄድ ለአስመራጭ ኮሚቴው አስፈላጊውን ትበበር ያደርጋል **አንቀጽ 33፡- አስመራጭ ኮሚቴ** ከምርጫው ቀን አንድ ወር በፊት ቦርዱ 5 አባላት ያሉት ያስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል ኮሚቴውም የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል

1. የአስመራጭ ኮሚቴው ፍላጎት ችሎታና ብቃት ያላቸውን አባላት ጥቆማ ከአባላት ይቀበላል

2. የአስመራጭ ኮሚቴው የተጠቋሚወችን የሙያ ብቃትና ያላቸውን ፈቃደኛነት ካጣራ በኋላ ስም ዝርዝርና የሚወዳደሩበትን የሥራ ዘርፍ ለአባላት ይፋ ያደርጋል
3. ኣጩ ተወዳዳሪዎች በመገናኛ ብዙሃን ራሳቸውን ኣንዲያስተዋውቁ ከተውዳዳሪውቻቸው ጋር ክርክር ኣንዲያደርጉ ይደረጋል
4. ጠቅላላ ጉባኤውን በመጥራት ምርጫው በግልጽ ይካሄዳል፣አብላጫ ድምጽ ያገኙ ኣጩዎች አሸናፊ ይሆናሉ ውጤቱም ለጠቅላላ አባላቱ ይገለጻል
5. የአስመራጭ ኮሚቴው ትክክለኛ የሆነና አድሎ የሌለበት ምርጫ መካሄዱን ያረጋግጣል የድምፅ አቆጣጠሩና ውጤቱም ለአባላቱ በትክክለኛ መገለጹን ያረጋግጣል ለተመራጮቹም ለተመረጡበት ዓላማ እንዲዘጋጁ ያደርጋል

**<u>አንቀጽ 34 ፡- የቦርድ አባላት አመራረጥ</u>** የቦርድ፣ የኦዲትና የቁጥጥር አገልግሎት አባላት ምርጫ በየ3 ዓመት በ---------------- ወር የመጀመሪያው ቅዳሜ ይከናወናል

**<u>አንቀጽ 35 ፡- የአገልግሎት ዘመን</u>** የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎአንጀለስ ማንኛውም በጠቅላላ ጉባኤው የተመረጡ የቦርድና የኦዲት ቁጥጥር የአገልግሎት ዘመን አራት (3) ዓመት ነው። በድጋሚ ለመወዳደር የሚፈልጉ መሪዎች ወይም ከተጠቆሙ ለ 2ኛ ጊዜ ለመወዳደር ይችላሉ

ማንኛውም የኮሚቴ ዓባል በተከታታይ ከሁለት ጊዜ በላይ ለምርጫ መወዳደር አይችልም፣

**<u>አንቀጽ 36፡- ይህ መተዳደሪያ ደንብ የሚሻሻልበት ሁኔታ</u>** ይህ መተዳደሪያ ደንብ እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻልና ሊለወጥ ይችላል

1. መተዳደሪያ ደንቡ የሚቀየረው (የሚሻሻለው) ከቦርዱ ዓባላት 2/3ኛው ከጠየቁና፣ ጥያቄው ቢያንስ በስብሰባው ላይ ከተገኙት የጠቅላላ ጉባኤ ዓባላት 2/3ኛው ከተስማሙበት ብቻ ነው።

**<u>አንቀጽ 37፡- የማሕበሩ መፍረስ</u>** ማሕበሩን ለማፍረስ ወይም ለመዝጋት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ይሆናል፡

1. ከጠቅላላ አባላቱ (3/4) ሶስት አራተኛው በአንድነት ተስማምተው መፍረሱን ሲያጸድቁ ብቻ ነው
2. ይህ ከሆነና ማሕበሩ እንዲፈርስ ከተወሰነ ማሕበሩ ያሉበትን እዳዎችና ህጋዊ ግዴታዎች ተጣርተው ያልተከፈሉ እዳዎች ካሉ ለባለ እዳው ተከፍሎ የሚቀረው ገንዘብና ንብረቶች በካሊፎርኒያ ግዛት ውስጥ ላሉ የዚሁ ማሕበር አይነት ተመሳሳይ ዓላማ ለሚያካሂዱ በጎ አድራጊ ድርጅቶች ይከፋፈላል።

**<u>አንቀጽ 38፡- መተዳደሪያ ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>** ይህ መተዳደሪያ ደንብ ከ------- ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**<u>አንቀጽ 39፡-ትርጓሜ</u>** ትርጉም ይህ ወደ አማርኛ የተተረጎመው መተዳደሪያ ደንብ ከኣንግሊዘኛው ሰነድ ጋር የሚያሻማ ወይም የማይጣጣም ትርጉም ሲኖረው የአማርኛው ሰነድ ሃሳብ የጸና ይሆናል።